January 3, 2005

ለኢትዮጵያ ሕብረተሰብ ማኅበር በኤድመንተን አባላት፤

ከመተዳደሪያ ደንብ አሻሻይ ኮሚቴ

ጉድዩ፡ <u>የመተዳደሪያ ደንብ ማሻሻያ ረቂቅን ስለማጠናቀቅ</u>

ዉድ የማኅበሩ አባላት ፡

እኛ ስማችን ከግርጌ የተመለከተዉ ግለሰቦች የስራ አስፈጻሚ ኮሚቴዉ ሰብስቦ የማኅበሩን መተዳደሪያ ደንብ ማሻሻያ እንድናረቅ ኃላፊነት ከሰጠን March 2004 ጀምሮ በጠቅላላዉ 15 ስብሰባዎችን በማድረግ የማሻሻያ ረቂቁን ስራ በ January 2, 2004 አጠናቀናል። የስራ አስፈፃሚ ኮሚቴዉ ስለሰጠን አንዳንድ ጠቃሚ ሃሳቦች በዚህ አጋጣሚ እናመሰግናለን። የማሻሻያ ረቂቁን ከዚህ ደብዳቤ ጋር አባሪ አድርገን አቅርበናል።

የተሻሻለዉ መተዳደሪያ ደንብ በአወቃቀርና በይዘቱ ከጥንቱ መተዳደሪያ ደንብ በሰፊዉ ይለያል። ተደጋጋሚነት ያላቸዉን አንቀጾች አዉጥተናል፤ ተመሳሳይ ይዘት ያላቸዉን አዳብለናል፤ በርካታ አዳዲስ አንቀጾችን ጨምረናል።

ዋና ዋናዎቹን ለዉጦች/ማሻሻያዎች ለመጥቀስ ያህል፥

- የማኅበሩ ስም "በኤድመንተን የኢትዮጵያዉያን - ካናዳዉያን ሕብረተሰብ ማኅበር" እንዲባል፤
- የጠቅላላ ጉባዔ ስብሰባ ምልዓተ ጉባዔ የሚሆንባቸዉ ሁኔታዎች እንደስብሰባዉ አጀንዳ የተለያየ እንዲሆን፤
- ማኅበሩ 13 አባላት ያሉት የዳይሬክተሮች ቦርድ እንዲኖረዉና ይህም ቦርድ ሰፊ ስልጣን ያለዉ የማኅበሩ የበላይ አስተዳዳሪ እንዲሆን፤
- የማኅበሩ ንዑሳን ኮሚቴዎች ሁሉ በምርጫ ሳይሆን በስራ አስፈጻሚ ኮሚቴዉ እንዲቋቋሙ፤
- ተግባራቱ በደንቡ ዉስጥ የተገለጹ የልማትና የእርዳታ ኮሚቴ እንዲቋቋም
- ተግባራቱ በደንቡ ዉስጥ የተገለጹ የሴቶች ጉዳይ ኮሚቴ እንዲቋቋም
- የሂሳብና ንብረት ኃላፊነት ለሁለት እንዲከፈል ሆኗል -- የሂሳብ ሹምና የገንዘብ ያዥ/ንብረት ክፍል ሃላፊ
- የገንዘብ ያዥ/ንብረት ክፍል ሃላፊ ህንፃና ሌሎች ቋሚና ተንቀሳቃሽ ንብረቶችን በተመለከተ ሃላፊ እንዲሆን፤
- የሰብአዊ መብት ጉዳዮች በኮሚቴ ደረጃ ሳይሆን በስራ አስፈጻሚ ኮሚቴዉ ም/ሊቀመንበር ኃላፊነት ስር እንዲዉል፤
- የስራ አስፈጻሚ ኮሚቴዉ በተጨማሪ እንድናያቸዉ የጠየቀን ጉዳዮች (የግል ኢንፎርሜሽንን ስለመጠበቅ፥ ስለ አመታዊ በአላት አከባበር፥ ስለመምረጥና መመረጥ መብቶችና ግዴታዎች) በመተዳደሪያ ደንቡ ዉስጥ በተለያዩ ቦታዎች ተካተዋል።
- የስልጣን ዉጣ ተዋረድና የኃላፊነት ገደቦች በግልጽና ተቃርኖን በማይፈጥሩ ሁኔታ ተቀምጠዋል።
- የማኅበሩን ዋና አላማዎች ከግብ ለማድረስ የሚረዱ የተግባር ስልቶች ( Strategies) በአባሪነት በመጨረሻ ተመልክተዋል።

ለወደፊት፥ የዚህ መተዳደሪያ ደንብ ሙሉ የእንግሊዝኛ ትርጉም ተዘጋጅቶ ለወጣቶችና አማርኛ ለማንበብ ለሚቸገሩ ሁሉ እንዲቀርብ እናሳስባለን። በተጨማሪም፥ የመተዳደሪያ ደንቡን በአጭር መልክ (Summary) አዘጋጅቶ ለሚመለከታቸዉ የመንግስት ክፍሎች እንዲቀርብ፤ እንዲሁም ስለማኅበሩ ማወቅ ለሚፈልጉ ሁሉ በማኅበሩ ዌብ ሳይትና በጽሁፍ አማካይነት እንዲቀርብ እናሳስባለን።

የተሰጠን ኃላፊነት ሕብረተሰባችንን በምንችለዉ አቅምና መንገድ ለመርዳት የምንችልበትን መድረክ ስለፈጠረልን ስራዉን ጀምረን የጨረስነዉ በሙሉ ልብና ደስታ ነዉ፤ ስለተሰጠን እድልም እናመሰግናለን፤፤

የመተዳደሪያ ደንብ አሻሻይ ኮሚቴ አባላት፥

- ተስፋዬ አያሌዉ — - አጥናዉ አይተንፍሱ — - ሺፈራዉ አ. አድሉ (ሰብሳቢ)
- አብርሃም ካሳዬ — - መኮንን በላይነህ
- ቤዛ አድማሱ — - ጥበቡ ተገኝ

# የኢትዮጵያ ሕብረተሰብ ማህበር በኤድመንተን

# ማስታወቂያ

የኢትይጵያ ሕብረተብ ማህበር February 6/2005 2:0-6:0 PM አጠቃላይ ስብሰባ ስለጠራ በዚሁ ቀንና ሰዓት የስብሰባው ተካፋይ እንዲሆኑ በትህትና ጥሪውን ያስተላልፋል

## የስብሰባው አጀንዳዎች፥

1 የአመቱ አጠቃላይ የስራና የሂሳብ ሪፖርት
2 ተሻሽሎ የቀረበውን የማህበሩን መተዳደሪያ ደንብ መመልከት
ቀደም ሲል የተመሰረተዉ የህገ-ደንብ አጥኝ ኮሚቴ ሥራዉን አጠናቆ ያቀረበልንን በእናንተ በአባላት እንዲታይ ከዚህ አባሪ ደብዳቤ ጋር በማያያዝ ልከናል ፡፡

3 የአስመራጭ ኮሚቴን መምረጥ

## ተጨማሪ ማስታወቂያ

ማህበራችን ያወጣቸውን የስራ እቅዶችና በተግባርም እየተሰሩ ያሉትን አበይት ክንዋኔዎች ለማስተዋወቅ ከ January 15/2005 ጀምሮ ዝወትር በሚቀጥሉት ሰዓታትና ቀናት የማህበሩ ጽህፈት ቤት ክፍት ይሆናል፡፡

ቅዳሜ ከቀኑ 2-6 ሰአት

እሁድ ከቀኑ 2-6 ሰአት

ከላይ በተመለከቱት ጊዜያቶች ከዚህ በታች የተመልከቱትን ፖሮግራሞች ለመከታተልና ልመረዳት እንደሚችሉ ያሳስባል ፡፡

1.የወጠቶች ጉዳይ

2.የሴቶችና የቤተሰብ ጉዳይ

3.የኮምፒዩተርና የኢንተርኔት አጠቃቀም

4.የልጆች የባህል ትምህርትና የመሳሰሉትን

**ለነኝህ ፕሮጀክቶች መሳካት አስተቃጽኦ ላድረገልን ድርጅት ለዋይልድ ሮስ ፋውንዴሽን (Wild Rose Foundation) ከልብ የመነጨ ምስጋናችንን እናቀርባለን**

የማህበሩ የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ፡፡

# የኢትዮጵያዉያን-ካናዳዉያን ህብረተሰብ ማኅበር በኤድመንተን

## መተዳደሪያ ደንብ

የካቲት 1997 (February 2005) ተሻሽሎ ተጻፈ

ኤድመንተን ፥ አልበርታ

ሠ. የሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ማለት የማኅበሩን የዕለት-ተዕለት ተግባር የሚያከናዉንና ማኅበሩን ወክሎ በአንቀጽ 17 መሰረት ስለማኅበሩ የሚሰራ፥ በአባላት ጠቅላላ ጉባኤ ተመርጦ የሚቋቋም የሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ማለት ነዉ።

ረ. የማኅበሩ አባል ማለት ማኅበሩ የተቋቋመበትን ዓላማ የሚያምን/የምታምን፥ የሚደግፍ/የምትደግፍ፥ የማኅበሩን ዓላማ ግብ ለማድረስ የግሉን/የግሏን አስተዋፅኦ የሚያደርግ/የምታደርግ፥ በማኅበሩ ሕግና ደንብ መሰረት የማኅበሩ አባል የሆነ/የሆነችና አመታዊ የአባልነት ክፍያን ያለማቋረጥ የሚከፍል/የምትከፍል ኢትዮጵያዊ-ካናዳዊ ማለት ነዉ።

ሰ. ፕሬዘዳንት ማለት የማኅበሩ ቦርድ ሰብሳቢ ማለት ነዉ።

ሸ. ሊቀመንበር ማለት የማኅበሩ የሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ሰብሳቢ ማለት ነዉ።

ቀ. ጊዜያዊ የምርጫ አስፈፃሚ ኮሚቴ ማለት የማኅበሩን ቦርድ አባላትና የሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ አባላትን እንዲሁም ለማኅበሩ ተግባር መከናወን አስፈላጊነት የሚኖራቸዉን ጊዜያዊና ቋሚ ኮሚቴዎችን በዚህ መተዳደሪያ ደንብ ዉስጥ በተለያዩ ቦታዎች በተደነገጉት ደንቦች መሰረት በጠቅላላ ጉባኤዉ የሚያስመርጥ የማኅበሩ ጊዜያዊ የምርጫ አስፈፃሚ ኮሚቴ ማለት ነዉ።

በ. የክብር አባል ማለት በኤድመንተን የተቋቋመዉ የኢትዮጵያዉያን-ካናዳዉያን ህብረተሰብ ማኅበር ዓላማ የሚደግፍ/የምትደግፍ፤ለዓላማዉም ግብ መድረስ ማቴሪያላዊና ሃሳባዊ አስተዋፅኦ የሚያደርግ/የምታደርግ በማኅበሩ ሕግና ደንብ የማኅበሩ የክብር አባል የሆነ ሌላ ዜጋ ማለት ነዉ።

ተ. የኦዲት ኮሚቴ ማለት በጠቅላላ ጉባኤ የሚመረጥ የማህበሩን የገንዘብ፥ የሃብትና የንብረት አያያዝ የሚመረምር የኦዲት ኮሚቴ ማለት ነዉ።

ቸ. አረካካቢ ኮሚቴ ማለት የሽግግር ጊዜ የገንዘብ፥ የሃብትና የንብረት አረካካቢ ኮሚቴ ማለት ነዉ።

ኀ. ተሳታፊ ግለሰብ ማለት የማኅበሩ አባል ሳይሆን/ሳትሆን የስራ አስኪያጅ ኮሚቴዉ በሚጠይቀዉና በሚፈቅደዉ መሰረት በማህበሩ የሰብአዊ፥ የባህልና ስፖርት እንቅስቃሴ በፈቃደኝነት የሚሳተፍ/የምትሳተፍ ኢትዮጵያዊ-ካናዳዊ ወይም ሌላ ዜጋ ማለት ነዉ።

**አንቀጽ 2 የማኅበሩ መቋቋም**

2.1 በካናዳ፥ አልበርታ ክፍለሀገር የማኅበሮችን ሕግና ደንብ በመከተል፥ በኤድመንተን ከተማ ዉስጥ የኢትዮጵያዉያን-ካናዳዉያን ህብረተሰብ ማኅበር አቋቁመናል።

2.2 ከላይ በአንቀጽ 2.1. የተቋቋመዉ የኢትዮጵያዉያን-ካናዳዉያን ህብረተሰብ ማኅበር ጽ/ቤት መቀመጫዉ በአልበርታ ክፍለሀገር በኤድመንተን ከተማ ዉስጥ ይሆናል።

## ክፍል ሁለት

**አንቀጽ 3 የማኅበሩ ዓላማ**

3.1 በኢትዮጵያዉያን መካከል የመተሳሰብ፥ የመተባበርና በፍቅር አብሮ የመኖር ባህል ለማዳበር፤ እንዲሁም ባለንበት ቦታ ችግሮቻችንን በጋራ መቋቋም እንድንችል ለማድረግ፤

3.2 በኤድመንተንና አካባቢዋ የሚኖሩና አዲስ የሚመጡ ኢትዮጵያዉያን-ካናዳዉያን በኢኮኖሚ፥ በማኅበራዊ ኑሮ፥ በሥራ፥በትምህርትና በሌሎች ጠቃሚ መስኮች የሚረዱበትን መንገድ እያጠና ተግባራዊ ለማድረግ፤

3.3 ታሪካችንን፥ባህላችንንና ቋንቋዎቻችንን እንዳንዘነጋና ለተተኪዉም ኢትዮጵያዉያን ትዉልዶች ለማስተላለፍ ቤተሰቦች የሚያደርጉትን ጥረት ለማገዝ፥ ብሎም ንቁ ተሳትፎ ለማድረግ፤

3.4 ስለትዉልድ አገራችን በአሁኑ ጊዜ በዓለም ዙሪያ የተሳለዉን አሳዛኝና አፍራሽ ገጽታ ለመቀልበስ አኩሪ ታሪካችንን፥ ዉብ ባህሎቻችንና ማራኪ የሆኑ የተፈጥሮና ሰዉ ሰራሽ መስህቦቻችንን በትጋት ለሌሎች ዜጎች ለማስተዋወቅ፤

3.5 በአልበርታ፥በሌሎች የካናዳ ክፍለሀገራትና በሰሜን አሜሪካ እንዲሁም በተለያዩ አህጉራትና ኢትዮጵያ ዉስጥ ከሚኖሩ ኢትዮጵያዉያን ጋር፥ ከዕርዳታ ሰጪ ድርጅቶች፥ከሰብዓዊ ድርጅቶች፥ ማህበራዊ አገልግሎት ከሚሰጡ ድርጅቶች እንድሁም ከባህላዊ፥ ስነጥበባዊና ኪነጥበባዊ ቡድኖችና ግለሰቦች ጋር ግኑኝነት በመፍጠር ኤድመንተን ከሚኖሩ ኢትዮጵያዉያን-ካናዳዉያን ጋር ለማስተዋወቅና ግኑኝነትን ለማዳበር፤

3.6 ካናዳ በብዙ ባህላዊ ማሕበረሰቦች ስብጥር የተገነባች አገር እንደመሆኗ መጠንና፥ የኢትዮጵያዉያን-ካናዳዉያን ማሕበረሰብም የነዚሁ ማሕበረሰቦች አንደኛዉ አካል እንደመሆኑ መጠን፥ በኤድመንተን ዉስጥ ካሉ፥ ተመሳሳይ ይዘትና ዓላማ ካላቸዉ ማኅበራትና ድርጅቶች ጋር የስራና የደብዳቤ ግንኙነት በመፍጠር ኢትዮጵያዉያን-ካናዳዉያን ከሌሎቹ ማሕበረሰቦች ጋር እኩል ተሳታፊና ገንቢ ሕብረተሰቦች እንዲሆኑ ለመጣር፤

3.6 በኢትዮጵያም ዉስጥ ሆነ ከኢትዮጵያ ዉጪ በሚኖሩ ኢትዮጵያዉያን ላይ ለሚደርሱ የተፈጥሮና ሰዉ ሰራሽ አደጋዎች፥ችግሮች እንዲሁም የሰብዓዊ መብቶች መጣስና የኢሚግሬሽን ጉዳዮች መፍትሔ ለመፈለግና ሲቻልም ሰብዓዊ ፥ ሞራላዊና ማቴሪያላዊ ዕርዳታ በወቅቱ ለማበርከት፤

3.7 የኢትዮጵያን ባህላዊና ታሪካዊ ቅርሶች በማሰባሰብ በኤድመንተን ለኢትዮጵያዉያን ትዉልዶችና ለሌሎች ዜጎች ለማስተዋወቅ፤

3.8 በካናዳና በሌሎች አገሮች የሚኖሩ ኢትዮጵያዉያን በሳይንስ፥ በቴክኖሎጂ፥ በኪነጥበብ፥ በስነጠበብ፥ በስፖርትና ሌሎች መስኮች የሚያደርጉትን አስተዋጽአና ግኝት ለማስተዋወቅ፤

## ክፍል ሶስት

**አንቀጽ** 4 **የተግባር ስልቶች** (Strategies)

ከላይ በክፍል ሁለት አንቀጽ 3 ስር የተመለከቱተን የማኅበሩን አላማዎች ለማራመድ ማኅበሩ ቀጥሎ የተዘረዘሩትንና ሌሎች በቦርዱ የሚጸድቁ ጠቃሚ ስልቶችን ይጠቀማል።

4.1 ይህ የማኅበሩ መተዳደሪያ ደንብ በጠቅላላ ጉባዔዉ ጸድቆ በስራ ላይ ሲዉል፥ ከአልበርታ መንግስት የማሕበረሰቦች ደንብ (Societies Act S-18) ጋር ተቀናጅቶ እንዲሰራ ያደርጋል።

4.2. የማኅበሩ አሰራር ዲሞክራሲያዊ ማዕከላዊነትን የተከተለ ይሆናል። ስብሰባዎች ፓርላማዊ አሰራርንና በካናዳ ዉስጥ ታዋቂ የሆነዉን **"Roberts Rules of Order"** መመሪያ የተከተሉ ይሆናል። ማኅበሩ አባላቱ ከዚህ አሰራር ጋር እንዲተዋወቁ ትምህርታዊ ሴሚናሮችን እንዳስፈላጊነቱ ያዘጋጃል።

4.3 ማኅበሩ በኢትዮጵያዉያን-ካናዳዉያን መካከል የመተሳሰብ፥ የመረዳዳትና አብሮ የመኖር ባህልን ለማዳበር በአመት አንድ ቀን "የኢትዮጵያዉያን-ካናዳዉያን" ቀን የተሰኘ በዓል ያዘጋጃል። ታዋቂ እንግዶችንም በመጋበዝና ንግግር እንዲያደርጉ በማድረግ አባላቱን ለዉጤታማ ኑሮ ይቀሰቅሳል፤ ያበረታታል። ባህላዊ ትርኢቶችን ያቀርባል። በዚህም በዓል ላይ ለማህበሩና ለኢትዮጵያ/ኢትዮጵያዉያን ልዩ አስተዋጽኦ ላደረጉ ግለሰቦች፥

- ሽልማቶችን ይሰጣል፤
- ፎቶግራፋቸዉ በማህበሩ ጽሕፈት ቤት አዳራሽ ዉስጥ እንዲሰቀሉ ያደርጋል፤

4.4 በማንኛዉም ኮሚቴ አባልነት ሲሰራ የላቀ ትጋትን ያሳዬ/ዉጤት ያስገኘ አንድ አባል "የዓመቱ ልዩ ተመራጭ" የሚል ስም ተሰጥቶት/ተሰጥቷት ፎቶግራፉ/ፎቶግራፏ በጽሕፈት ቤቱ አዳራሽ ዉስጥ ይሰቀላል።

4.5 ታሪካችን፥ አኩሪ ባህሎቻችንና ቋንቋዎቻችን በተለይ በወጣቶች እንዳይረሳና በካናዳ የተወለዱ ወይም ያደጉ ልጆቻችን እንዲማሩት ለማድረግ እንዲረዳ
- የቋንቋና የባህል ት/ቤት መክፈት
- የኢትዮጵያን ታሪክና ባህል ሊያሳዩ/ሊያስረዱ የሚችሉ ቅርሶችንና ጽሁፎችን የያዘ ቤተ መዘክር/ቤተ መጽሕፍት መክፈት
- በታዳጊ ወጣቶች የሚካሄድ የባህልና የሙዚቃ ክፍል ማቋቋም

4.6 ማኅበሩ አቅሙ የፈቀደዉን ያህል የኢንተርኔት ግንኙነት ያላቸዉ ኮምፒተሮች በቤተ-መጽሕፍት ዉስጥ በማስገባት ለአባላቱ ጥቅም ያዉላል። የተለያዩ ጠቃሚና ትምህርታዊ የሆኑ ጋዜጦችንና፥ መጽሔቶችን ያቀርባል።

4.7 ማኅበሩ ተመሳሳይ አላማና ይዘት ካላቸዉ ባህላዊ ማህበርሰቦች ማኅበራት ( Multicultural Organizations) በተለይም ቀጥሎ ከተጠቀሱት ጋር ግንኙነት ያዳብራል፤ ልምዶችን ይቀስማል።
- የአፍሪካ ማህበራት ድርጅት አባል በመሆን ድርጅቱን ለማሳደግ ይተባበራል፤
- ከካሪቢያንና ከሌሎች የጥቁር ሕዝቦች ባህላዊ ድርጅቶች ጋር የቀረበ ግንኙነት ይፈጥራል፤
- በአመት አንድ ጊዜ በሚካሄደዉ የጥቁሮች ታሪክ ወር (Black History Month) በዓል በቀጥታ ተሳታፊ በመሆን የኢትዮጵያን የታሪክ አስተዋጽኦ ያስተዋዉቃል፤

4.8 የማኅበሩን የገንዘብ አቅም ለማጠንከር በአመት አንድ ጊዜ የገንዘብ መሰብሰቢያ (Fund Raising) ቀን ያዘጋጃል።

4.9 በተለያዩ ኮሚቴዎች ያገለገሉ አባላት በስራ ዘመናቸዉ ፍጻሜ ላይ የሚነሱት የጋራ ፎግራፍ በማኅበሩ አልበም ዉስጥ ይቀመጣል/ በጽሕፈት ቤቱ አዳራሽ ዉስጥ ይሰቀላል። በቦርዱ ፕሬዚዳንትነትና በስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ሊቀመንበርነት ያገለገሉ የግል ፎቶግራፎች በጽሕፈት ቤቱ አዳራሽ ዉስጥ ይሰቀላል።

4.10 ማኅበሩ የሚያከብራቸዉ አመታዊ በአሎች በማኅበሩ የስራ ካሌንደር ላይ በማዉጣት አባላት እንዲያዉቁትና እንዲጠብቁት በጽሕፈት ቤቱ አዳራሽ ዉስጥና፥ በማኅበሩ ዌብ ሳይት ይለጠፋል፤

4.11 ማኅበሩ ወጣቶች እንዲቀራረቡ፥ ሕብረታቸዉን እንዲያጠነክሩ፥ ሃሳባቸዉንም እንዲለዋወጡና መልካም ጊዜ እንዲያሳልፉ ሁኔታዎችን ያመቻቻል፤ በአመት አንድ ቀን "የወጣቶች ቀን" እንዲያዘጋጁ ይርዳል።

4.12 ማኅበሩ አባላቱ በኑሮ ደረጃ የሚሻሻሉበትን መንገድ ለማስፋት የሚረዱ ትምህርቶችን (Work Shops) አቅም በፈቀደ መጠን ያዘጋጃል። ለአባላቱ የስራ እድል ሊፈጥሩ የሚችሉ ማህበራዊ (ትርፍ-አስገኚ ያልሆኑ (Non-profit) ፕሮጀክቶችን እያጠና ከመንግስት በኮንትራት ለማግኘት ይጥራል።

4.13 ማኅበሩ የመንግስትና የመንግስት ያልሆኑ ከማኅበሩ ጋር በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ግንኙነት ሊኖራቸዉ የሚችሉ ድርጅቶች የሚመሩ ባለስልጣኖችን ወይም ተወካዮችን በመጋበዝ ማህበሩን ያስተዋዉቃል።

## ክፍል አራት

### አንቀጽ 5 የማኅበሩ አባላት

5.1 ዕድሜያቸዉ ከ18 ዓመት በላይ የሆነ ኢትዮጵያዉያን-ካናዳዉያን ከላይ በአንቀጽ 2.1 ና 2.2 መሠረት በተቋቋመዉ ማኅበር አባል መሆን ይችላሉ።

5.2 በትዉልዱ ኢትዮጵያዊ ያልሆነ/ያልሆነች ዜጋ በማህበሩ ህግና ደንብ መሰረት የማህበሩ የክብር አባል መሆን ይችላል/ትችላለች።

**አንቀጽ 6 ተሳታፊ ግለሰብ**

ኢትዮጵያዉያን-ካናዳዉያንም ሆኑ ሌሎች ዜጎች በአንቀጽ 1(ቸ) መሰረት የማኅበሩ ተሳታፊ ግለሰብ መሆን ይችላሉ።

## ክፍል አምስት

**አንቀጽ 7 የአባላትና ተሳታፊ ግለሰቦች ምዝገባ**

ከላይ በአንቀጽ 5 ና 6 በተደነገገዉ የማኅበሩ ሕግና ደንብ መሠረት የማኅበሩ አባል፥ የክብር አባልና ተሳታፊ ግለሰብ የሆኑ ሁሉ በማህበሩ መዝገብ ዉስጥ መመዝገብ አለባቸዉ።

## ክፍል ስድስት

**አንቀጽ 8 የአባልነት ክፍያ**

8.1 ከላይ በአንቀጽ 5.1 መሠረት የማኅበሩ አባል የሆነ/የሆነች ቦርዱ ወስኖ ጠቅላላ ጉባኤዉ የሚያፀድቀዉን የምዝገባና አመታዊ ክፍያ መክፈል አለበት/አለባት።

8.2 ከላይ በአንቀጽ 5.2 መሠረት የማኅበሩ የክብር አባል የሆነ/የሆነች በቦርዱ አስተያዬት መሰረት ጠቅላላ ጉባኤዉ የሚወስነዉን የክብር አባልነት ክፍያ መክፈል አለበት/አለባት።

## ክፍል ሰባት

**አንቀጽ 9 ከማህበሩ ስለመሰናበት**

9.1 ማንኛዉም የማኅበር አባል በማንኛዉም ጊዜ በራሱ/በራሷ ፈቃድ ከማኅበሩ የመዉጣት መብቱ/መብቷ የተጠበቀ ነዉ፤ ማኅበሩን የሚለቅበትን/የምትለቅበትን ምክንያት ቢቻል በጽሁፍ ለማኅበሩ ማቅረብ ይችላል/ትችላለች። ከማህበሩም የምስክርነት ወረቀት መጠየቅ ይችላል/ትችላለች።

9.2 በአንቀጽ 11.1 መሰረት የአባልነት ዓመታዊ ክፊያን በሦስት ወራት ጊዜ ዉስጥ ሳይከፍል/ሳትከፍል የቀዬ/የቀየች አባል፥ ወይም የክብር አባል ከማኅበሩ አባልነት ይሰረዛል/ትሰረዛለች።

9.3 ማንኛዉም አባል፥ ወይንም የክብር አባል በተለያዩ ምክንያቶች ኤድመንተንንና አካባቢዋን ለቆ/ለቃ ከሄደ/ከሄደችና ከአንድ ዓመት በላይ ለሆነ ጊዜ ከማህበሩ ጋር ምንም አይነት ግንኙነት ሳይኖረዉ/ሳይኖራት ከቆየ/ከቆየች ከአባልነት በፈቃዱ/በፈቃዷ እንደለቀቀ/እንደለቀቀች ይቆጠራል።

9.4 ከማኅበሩ ዓላማ ዉጪ በመሆን በማንኛዉም መንገድ ማኅበሩን የሚጎዳና የሚያዳክም ወይንም በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ አባላትንና የአባላትን ጥቅም የሚጎዳ ድርጊት በሚፈጽም/በምትፈጽም አባል ወይም የክብር አባል ላይ ጠቅላላዉ ጉባኤ አስፈላጊዉን ሕጋዊ እርምጃ እስኪወስድ ድረስ የስራ አስፈጻሚ ኮሚቴዉ ጊዜያዊ የአባልነት እገዳ ሊያደርግበት/ሊያደርግባት ይችላል።

9.5 ማንኛዉም አባል ወይም የክብር አባል ከማኅበሩ ሲሰናበት/ስትሰናበት፡

ሀ. ከማኅበሩ የተረከባቸዉን/የተረከበቻቸዉን ማንኛዉንም ሀብት፥ንብረት ወይም ሰነድ የስራ አስፈጻሚ ኮሚቴዉ እንደሁኔታዉ በሚወስነዉ የጊዜ ገደብ ዉስጥ ለማኅበሩ ማስረከብ አለበት/አለባት።

ለ. የማኅበሩን ሀብት፥ንብረት ወይም ሰነድ ሳያስረክብ/ሳታስረክብ ቢቀር/ብትቀር በካናዳ አልበርታ ሕግ መሰረት ተጠያቂ ይሆናል/ትሆናለች።

ሐ. ለመመዝገቢያና ለዓመታዊ ክፍያ የከፈለዉን/የከፈለችዉን ገንዘብ ወይም ለማኅበሩ የሰጠዉን ሀብትና ንብረት መጠየቅ አይችልም/አትችልም።

**አንቀጽ 10 ወደ ማኅበሩ ተመልሶ ስለመግባት**

ከማህበሩ አባልነት ወይም የክብር አባልነት የተሰናበተ ግለሰብ ወደማኅበሩ ለመመለስ በጽሑፍ ሲጠይቅ/ ስትጠይቅ በቦርዱ ዉሳኔ መሰረት ጠቅላላ ጉባኤዉ ሲያፀድቀዉ ወደማህበሩ ሊመለስ ይችላል/ትችላለች።

## ክፍል ስምንት

**አንቀጽ 11 . የአባልነት ግዴታ**

11.1 ማንኛዉም አባል ቦርዱ ወስኖ ጠቅላላ ጉባዔዉ የሚያጸድቀዉን አመታዊ የአባልነት ክፍያ መክፈል አለበት/ አለባት።

11.2 ማንኛዉም የክብር አባል የስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ የሚወስነዉን አመታዊ የአባልነት ክፍያ መክፈል አለበት/ አለባት።

11.3 እያንዳንዱ አባል የማህበሩን ህግና ዉስጠ ደንብ የማክበር፥ የማህበሩን ጠቅላላ መመሪያዎች፥ አላማዎችና ተግባሮች የማራመድ ግዴታ አለበት/አለባት።

11.4 ማንኛዉም አባል የአባልነት ጠቅላላ ስብሰባ ላይ እንዲሁም ተመርጦ/ተመርጣ ወይም ተመድቦ/ተመድባ በሚሰራበት/በምትሰራበት ኮሚቴ ስብሰባ ላይ የመገኘት ግዴታ አለበት/አለባት። አንድ አባል በአመት አንድ ጊዜ ከጠቅላላ ጉባዔ ሲቀር/ስትቀር የስልክ ጥሪ ይደረግለታል/ይደረግላታል፤ ለሁለተኛ ጊዜ ሲቀር/ስትቀር የወቀሳ ደብዳቤ ይላክለታል/ይላክላታል፤ ለሶስተኛ ጊዜ ሲቀር/ስትቀር ማኅበሩ አስፈላጊዉን ርምጃ ይወስዳል።

11.5 ማንኛዉም አባል፥ የክብር አባል፥ ወይም ተሳታፊ ግለሰብ፥ የፈቃደኝነት ግዴታዉን/ግዴታዋን በማወቅ ማኅበሩ በሚጠይቀዉ የሥራ ድርሻ የመሳተፍ ሃላፊነት አለበት/አለባት።ያለበቂ ምክንያት በተደጋጋሚ ሃላፊነታቸዉን በማይወጡ አባል፥ የክብር አባል፥ ወይም ተሳታፊ ግለሰቦች ላይ ማኅበሩ አስፈላጊዉን ርምጃ ይወስዳል።

## ክፍል ዘጠኝ

**አንቀጽ 12 የአባላት ጥቅም**

12.1 እያንዳንዱ አባል ማኅበሩን ለማጠናከር፥ለማጎልበትና ለማሳደግ ያቅሙንና የችሎታዉን አስተዋጽኦ ማድረግ መብቱም ግዴታዉም ሲሆን ከማኅበሩ የሚገኝ ጥቅምንም በእኩልነት የመካፈል መብት አለዉ።

12.2 እያንዳንዱ አባል ከላይ በማኅበሩ ዓላማ በአንቀጽ 3.2 በተመለከተዉ መሠረት ማኅበሩ በሚያደርገዉ የትምህርት፥የሥራና የማህበራዊ ኑሮ አገልግሎቶች ተጠቃሚ ይሆናል/ትሆናለች።

12.3 የማኅበሩ አባላትና ልጆቻቸዉ ባህላችንን፥ቋንቋዎቻችንንና ታሪካችንን እንዲያዉቁ ማኅበሩ የተለያዩ

ፕሮግራሞችንና አገልግሎቶችን ይሰጣል።

12.4 የማኅበሩ አባላት በሙያቸዉ ሥራ እንዲያገኙ ማኅበሩ የኢንፎርሜሽንና የድጋፍ ትብብር ያደርጋል።

12.5 ማኅበሩ ከተለያዩ መንግሥታዊና የግል ድርጅቶች ጋር (ለምሳሌ ከካናዳ የሰራተኛ ጉዳይ ክፍል (Employment Canada)፥ ኢምግሬሽን) በሚያደርገዉ የጠበቀ ግኑኝነት አባላት ተጠቃሚ ይሆናሉ።

12.6 ማኅበሩ በሚያካሂደዉ እንቅስቃሴ ፥ የኢኮኖሚ ጥቅሞች የሚያስገኙ የተለያዩ ሥራዎችን ለግለሰቦች መስጠት ቢፈልግ (ለምሳሌ ሄሪቴጅ በዓል) አባላት ቅድሚያ ተሰጥቶአቸዉ ተጠቃሚ እንድሆኑ ይደረጋል።

12.7 የማኅበሩ አባል የሆነ/የሆነች የጋብቻ ሥነ-ሥርዓት ሲፈጽም/ስትፈጽም ማኅበሩ እስከ $50 የሚያወጣ ስጦታ ያደርጋል።

12.8 የማኅበሩ አባል የሆነ/የሆነች፥ ልጅ ሲወልድ/ስትወልድ ማኅበሩ እስከ $25 የሚያወጣ ስጦታ ያደርጋል።

12.9 በማኅበሩ አባል ወይንም አብረዉ በሚኖሩ የቤተሰብ አባል ላይ የሞት አደጋ ቢደርስ ለአንዳንድ ወጮች መሸፈኛ እንዲሆን፥ ማኅበሩ $250 የማስተዛዘኛ ወጭ ይሰጣል። እንደአስፈላጊነቱም አባላትን በማስተባበር ተጨማሪ ርዳታ እንዲደረግ ጥረት ያደርጋል።

12.10 የማኅበሩ አባል እሥራት ሲያጋጥመዉ/ሲያጋጥማት በካናዳ አልበርታ ሕግ መሠረት ማኅበሩ አቅሙ በፈቀደ መጠን ሕጋዊና የተለያዩ እርዳታዎችን ያደርጋል።

## ክፍል አስር

### አንቀጽ 13 የማኅበሩ ድርጅታዊ አቋም

ከዚህ በላይ በአንቀጽ 2.1 የቋቋመዉ ይህ ማኅበር ከዚህ በታች የተመለከቱት ዋና አካሎች ይኖሩታል፤

13.1 **ጠቅላላ ጉባዔ፡** የማኅበሩ አባላት በምልዓት ወይም አብዛኛቸዉ የሚገኙበት ስብሰባ ጠቅላላ ጉባዔ ይባላል።

ሀ. በዚህም መሰረት፥ የመተዳደሪያ ደንብን ለማጽደቅ፥ለመለወጥ ወይም ምርጫ ለማካሄድ ቢያንስ የአባላት 2/3ኛ የተገኙበት ስብሰባ ምልዓት ጉባዔ ይሆናል። ይሁንና ለተጠቀሱት ጉዳዮች የተጠራ የመጀመሪያ ስብሰባ የሚፈለገዉን ቁጥር ሳያገኝ ቢቀር፥ በቀጣይ ስብሰባዎች ከአባላቱ 50 በመቶ በላይ ከተገኙ ጉባዔዉ እንደጠቅላላ (ምልዓተ) ጉባዔ ይቆጠራል።

ለ. ከላይ በ "ሀ" አንቀጽ 28(ሀ) ና አንቀጽ 31 ከተጠቀሱት አጀንዳዎች በስተቀር፥ የአባላቱ 51 በመቶ የተገኙበት ስብሰባ ምልዓተ ጉባዔ ይሆናል።

13.2 **ቦርድ፡** የዳይሬክተሮች ቦርድ ከታች በአንቀጽ 15(ሀ) መሰረት የሚቋቋም ይሆናል።

13.3 **የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ፡** የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ከታች በአንቀጽ 17(ሀ) መሰረት የሚቋቋም ይሆናል።

### አንቀጽ 14 ጠቅላላ ጉባኤ

ሀ. የማኅበሩ ሕግና ደንብ አዉጪና አጽዳቂ አካል ነዉ።

ለ. የቦርዱንና የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ አባላትን በአንቀጽ 15 (ሀ) መሰረት መርጦ ይሾማል።

ሐ. በጠቅላላ ጉባዔዉ የተመረጡትን የቦርድና የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ አባላትን የመሻር መብት አለዉ::

መ. የቋሚ ንብረት ሽያጭና ግዢን በተመለከተ ቦርዱ አጥንቶ ሲያቀርብ ዉሳኔ ያሳልፋል::

ሠ. በቦርዱ ለሚቀርቡት ጉዳዮች ዉሳኔና መመሪያ ይሰጣል::

## አንቀጽ 15 ቦርድ

ሀ. ከላይ በአንቀጽ 13.2 መሠረት 14 አባላት የሚኖሩት ቦርድ በጠቅላላ ጉባኤዉ ይቋቋማል:: ከአባላቱ ዉስጥ አራቱ (ከኢትዮጵያዊያን-ካናዳዊያን) የሃይማኖት ድርጅቶች የሚወከሉ ሲሆን፥ የቀሩት ከማህበሩ አባላት በጠቅላላ ስብሰባ የሚመረጡ ይሆናል:: በምርጫ ከሚሾሙት የቦርድ አባላት ቢያንስ ሁለቱ ሴቶች መሆን አለባቸዉ::[3]

ለ. ከሃይማኖት ድርጅቶች የሚወከሉት የቦርድ አባሎች የማኅበሩ አባል መሆን አለባቸዉ::

ሐ. ቦርዱ ኢትዮጵያዊ-ካናዳዊ የሆነ/የሆነች አንድ ፕሬዚዳንትና አንድ ጸሐፊ ይኖሩታል::

መ. የቦርዱ ፕሬዚዳንት በጠቅላላ ጉባዔዉ የተመረጠ/የተመረጠች ይሆናል/ትሆናለች::

ሠ. የሥራ አስፈጻሚዉ ኮሚቴ ሊቀመንበር የቦርዱ ፀሐፊ ናቸዉ::

ረ. የሌሎች የቦርዱ አባላት የሥራ ድርሻ በቦርዱ አባላት ይወሰናል::

ሰ. በጠቅላላ ጉባዔዉ ከሚመረጡት የቦርድ አባላት ዉስጥ 1/3ኛዉ በየአመቱ በአዲስ ተመራጮች ይተካሉ::[4]

## አንቀጽ 16 የቦርዱ ተግባር

ሀ. ለጠቅላላ ጉባኤዉ ተጠሪ በመሆን ማኅበሩ የተቋቋመለትን ዓላማና ተግባር ከግብ ለማድረስ ኃላፊነት የተሰጠዉ የማኅበሩ የበላይ ጠባቂና አስተዳዳሪ (መሪ) አካል ይሆናል::

ለ. የማኅበሩ ሕጎችና ደንቦች በትክክል መተርጎማቸዉንና መፈጸማቸዉን በበላይነት ይቆጣጠራል::

ሐ. ከላይ በ “ሀ” ና “ለ” መሠረት የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴዉ የተቀበለዉን ኃላፊነት በብቃት እንዲወጣ ያግዛል፤ ይቆጣጠራል:: ስራቸዉን በብቃት ለመወጣት ያልቻሉ የስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ አባላት ጉዳይ ከታች በአንቀጽ 18.2 (መ) መሰረት ሲደርሰዉ ጉዳዩን ይመረምራል፤ እንዳስፈላጊነቱም ጉዳዩን ለጠቅላላ ጉባዔዉ ከአስተያዬት ጋር ያቀርባል::

---

[3] የሴቶች ጉዳይ ኮሚቴ ተጠናክሮ መንቀሳቀስ በሚጀምርበትና፥ የኮሚቴዉ አባላት በሴቶች ምርጫ የሚወከሉበት ወቅት ሲደረስ በቦርዱ ዉስጥ የሚያገለግሉት ሴቶች ከሴቶች ጉዳይ ኮሚቴ በቀጥታ የሚወከሉ ይሆናሉ::

[4] ይህ ማሻሻያ ከጸደቀ በኋላ በሚኖረዉ የመጀመሪያ ዙር ምርጫ የቦርድ አባል ከሚሆኑት ዉስጥ 1/3ኛዉ በአንድ አመት መጨረሻ ላይ፥ ሌሎች 1/3ኛው ደግሞ በሁለተኛዉ አመት መጨረሻ ላይ በአዲስ ተመራጮች ይተካሉ፤ የቀሩት 1/3ኛ ተመራጭ የቦርዱ አባላት፥ ፕሬዚዳንቱን ጨምሮ የሶስት አመት ተርማቸዉን ይጨርሳሉ:: የቦርዱ ጸሃፊ የአገልግሎት ዘመን በአንቀጽ 16 (ሀ) መሰረት የሚወሰን ነዉ:: የትኞቹ አባላት በመጀመሪያዉ አመት ማብቂያ፥ የትኞቹ ደግሞ በሁለተኛዉ አመት ማብቂያ ለምርጫ መቅረብ እንዳለባቸዉ ፕሬዚዳንቱ የቦርዱ ጸሃፊ ጋር በመመካከር ይወስናል:: ከመጀመሪያዉ ዙር በኋላ የሚመረጡ የቦርድ አባላት በተለዬ ምክንያት ካላቋረጡ በስተቀር የሶስት ዓመት ተርም ይጨርሳሉ:: ከሐይማኖት ድርጅቶችና ለወደፊትም (በግርጌ ማስታወሻ 3 መሰረት) ከሴቶች የሚወከሉ የቦርድ አባላት የስራ ዘመን የሚወሰነዉ በሚወክሏቸዉ ክፍሎች ዉሳኔ ይሆናል::

መ. የማኅበሩ የመተዳደሪያ ደንቦች እንዲሁም ዓላማዎቹ እንዲዳብሩና ጥልቀት እንዲያገኙ ቦርዱ አዳዲስና የማሻሻያ ሃሳቦችን እያጠና ለጠቅላላዉ ጉባኤዉ ለመጨረሻ ዉሳኔ ያቀርባል።

ሠ. ከላይ በአንቀጽ 3.5 የተገለጹትን ዓይነት አበይት ጉዳዮችን በተመለከተ፥ በወቅቱ አስፈላጊ ጥናቶችን በማድረግና ዉሳኔ ላይ በመድረስ ለስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ መመሪያ ይሰጣል፤ እንደአስፈላጊነቱም ለጠቅላላዉ ጉባኤ እንዲቀርብ ያደርጋል።

ረ. ከላይ ስለማኅበሩ ዓላማ በአንቀጽ 3.4 እንደተጠቀሰዉ ማኅበሩ ከሌሎች ኢትዮጵያዉያን ግለሰቦች፥ ማኅበራትና ድርጅቶች ጋር የሚፈጥረዉ ግኑኝነት ከዘር፥ከፆታ፥ከሃይማኖትና ከወገናዊ ፖለቲካ ተጽዕኖ ነፃ መሆኑን ይቆጣጠራል።

ሰ. ከላይ በአንቀጽ 3.2 ለተጠቀሰዉ የማኅበሩ ዓላማ መሳካት ማኅበሩንና አባላትን የሚጠቅሙና የሚያጎለብቱ ማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ ፕሮጀክቶችን እያጠና ለስራ አስፈጻሚ ኮሚቴዉ መመሪያ ይሰጣል።

ሸ. በተለያዩ የማኅበሩ ኮሚቴዎች፥ ንዑሳን ኮሚቴዎች፥ የአመራር አባላትና የማህበሩ አባላት መካከል በሥራ ግኑኝነት የተነሳ የሚፈጠሩ አለመግባባቶችን የሥልጣን ተዋረዱን ጠብቆ ሲቀርብለት የማኅበሩን የመተዳደሪያ ደንብ መንፈስ በመመርኮዝ መፍትሔና መመሪያ ይሰጣል።

ቀ. በአንቀጽ 18.5 (ሀ) መሰረት የስራ አስፈጻሚ ኮሚቴንና የንዑሳን ኮሚቴዎችን ዝርዝር በጀቶች፥ እንዲሁም በአንቀጽ 17(ረ) መሰረት በየወቅቱ የሚከሰቱትን ከ$500 በላይ የሆኑ ወጪዎችን ያጸድቃል፤ አስፈላጊ የሆኑ የወጭ ስኬሎችን ያወጣል።

በ. የማኅበሩ ዓርማ ወይም መታወቂያዎች፥ ፎርሞች፥ ቅጾችና የስራ ሰነዶችና የማኅበሩ ልሳኖች (ምሳሌ፥ መጽሔቶች፥ ዌብ ሳይቶች) ስሞች ፥ የማኅበሩን ሁለንተናዊነት የሚያንጸባርቁ እንዲሆኑና ተጠንተዉ እንዲዘጋጁ፥ ያደርጋል፤ እንዳስፈላጊነቱም በጠቅላላ ጉባኤዉ እንዲጸድቁ ያደርጋል።

ተ. ከታች በአንቀጽ 17 (ኀ) መሰረት በስራ አስፈጻሚ ኮሚቴዉ የሚዘጋጀዉን አመታዊ አጠቃላይ የስራ ሪፖርት ተመልክቶ፤ ለጠቅላላ ጉባዔዉም እንዲቀርብ ያደርጋል።

## አንቀጽ 17 የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ

ሀ. ከላይ በአንቀጽ 13.3 መሰረት ዘጠኝ አባላት ያሉት አንድ የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ በጠቅላላ ጉባኤዉ ምርጫ ይቋቋማል። የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴዉ ቢያንስ አንድ የሴት አባል ይኖረዋል። የኮሚቴዉ የሥራ ዘመንም ሁለት ዓመት ይሆናል።

ለ. ከላይ በአንቀጽ 16 (ሀ) ና 16 (ሐ) መሠረት የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ተጠሪነቱ ለቦርዱ ይሆናል።

ሐ. በማኅበሩ መተዳደሪያ ደንብ እንዲሁም በጠቅላላ ጉባኤዉና በቦርዱ በሚሰጡት መመሪያዎችና ዉሳኔዎች መሠረት የማኅበሩን የዕለት ተዕለት ተግባር ይመራል፥ ያከናዉናል።[5]

መ. ከላይ በአንቀጽ 3.2 መሠረት በኤድመንተን ከተማ የሚኖሩና አዲስ የሚመጡ ኢትዮጵያዉያን ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ዕርዳታ የሚያገኙበትን ሥልት እያጠና በአጭርና በረጅም ጊዜ እቅድ ተግባራዊ ያደረጋል።

ሠ. ከላይ በአንቀጽ 3.4 ለተጠቀሰዉ የማኅበሩ ዓላማና ተግባር ቦርዱ በሚሰጠዉ መመሪያ መሠረት ከኤድመንተን ዉጪ ከሚኖሩ ኢትዮጵያዉያንና የኢትዮጵያዉያን ማህበራት ጋር የዳበረ ግኑኝነት ለመፍጠር ይጥራል።

---

[5] የስራ አስፈጻሚ ኮሚቴዉ የቦርዱን መመሪያ መቀበልና በተግባር ላይ ማዋል ይጠበቅበታል፤ የቦርዱን ዉሳኔ ወይም መመሪያ የማይቀበልበት ሁኔታ ከተፈጠረ ቦርዱ አስቸኳይ የጠቅላላ ጉባዔ ስብሰባ በመጥራት በጉዳዩ ላይ ያልወስናል።

መ. ሥራቸዉን በትክክልና በብቃት ወይም በተለዬ ምክንያት መወጣት ያልቻሉ የስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ አባላት ሲኖሩ ለቦርዱ በማቅረብ አስፈላጊዉን ዉሳኔ ያስወስናል።

ሠ. የንዑሳን ኮሚቴዎች መቋቋማቸዉንና ሥራቸዉን በትክክል ማከናወናቸዉን ያረጋግጣል።

ረ. ከገንዘብ ያዥ/ንብረት ክፍል ኃላፊ ጋር በመሆን ቼኮችን ይፈርማል።

ሰ. ከላይ በአንቀጽ 17(ኀ) መሠረት በየስድስት ወሩ ለቦርዱ የሥራ ሪፖርት ያቀርባል።

ሸ. በማኀበሩ የሥራ እንቅስቃሴ የተነሳ በአባላት፥ በንዑሳን ኮሚቲዎች ወይም በተመራጮች መካከል የሚፈጠሩ ቅራኔዎችንና አለመግባባቶችን በማኀበሩ ሕግና ደንብ መሰረት መፍትሔ ይሰጣል፤ በወቅቱ መፍትሔ መስጠትና ማግባባት ካልቻለ ከላይ በአንቀጽ 16(ሸ) መሠረት ጉዳዩን ለቦርዱ ያቀርባል።

ቀ. ለማህበሩ ለሚጻፉ ደብዳቤዎች ወቅታዊ ምላሽ ይሰጣል።

በ. ሌሎች ጠቅላላ ጉባኤዉና ቦርዱ የሚሰጡትን ኃላፊነቶች ያከናዉናል።

18.3 የማኀበሩ ም/ሊቀመንበር የሚከተሉት ተግባራት ይኖሩታል፤

ሀ. ሊቀመንበሩ በሌለበት ወቅት ሊቀመንበሩን በመተካት ከላይ በአንቀጽ 18.2 የተደነገጉትን በኃላፊነት ይሠራል።

ለ. ሊቀመንበሩ በችግር ወይም በሌላ ምክንያት ስራዉን መቀጠል ባይችል፥ ጠቅላላ ጉባዔዉ ተጠርቶ ሌላ ሊቀመንበር እስኪመረጥ ድረስ፥ የስራ አስፈጻሚ ኮሚቴዉን ስራ ይመራል፤ የቦርዱ ጸሀፊም ሆኖ ይሰራል።

ሐ. የልማትና እርዳታ ንዑስ ኮሚቴን ይመራል።

መ. ከፖለቲካ ወገናዊነት ነጻ በሆነ መንገድ በኢትዮጵያ የሚደረጉ ግልጽ የሰብዓዊ መብት ረገጣዎችን ይከታተላል፤ ለስራ አስፈጻሚ ኮሚቴዉም ያቀርባል። ሪፖርቱም ለቦርዱ ቀርቦ ሲጸድቅ ማኀበሩ የአቋም መግለጫዎችን ያወጣል።

ሠ. ከላይ በ "ሐ" ና "መ" የተመለከቱትን ኃላፊነቶች ለመወጣት፥ በአንቀጽ 17 (በ) መሰረት፥ እንዳስፈላጊነቱ የስራ አስፈጻሚ ኮሚቴዉ ጊዜያዊ ወይም ቋሚ ኮሚቴ እንዲያቋቁምለት ሊጠይቅ ይችላል።

ረ. በሊቀመንበሩ የሚሰጡትን ሌሎች የሥራ ተግባርና ኃላፊነት በመቀበል ይሠራል።

18.4 የማኀበሩ ዋና ፀሐፊ የሚከተሉት ተግባራት ይኖሩታል፤

ሀ. የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ስብሰባ አጀንዳዎች ከሊቀመንበሩ ጋር በመመካከር ያዘጋጃል፤ የስብሰባ ቃለ ጉባኤ ይይዛል።

ለ. የማኀበሩን የጽሕፈት ዶክመንቶችን፥ሰነዶችንና ማህተሞችን ይይዛል።

ሐ. የማኀበሩን የዕለት ተዕለት የጽሕፈት ሥራ ይሠራል፤ ለማህበሩ የተላኩ ደብዳቤዎች ወቅታዊ ምላሽ እንዲያገኙ አስፈላጊዉን ጥረት ያደርጋል።

መ. ከማኀበሩ አመራር አባላት የሚመጡትን መልዕክቶች ለአባላት ያስታዉቃል።

ሠ. ሊቀመንበሩና ም/ሊቀመንበሩ በሌሉበት የስራ አስፈጻሚ ኮሚቴዉን ይመራል። ሊቀመንበሩና ም/ሊቀመንበሩ

ስራቸዉን መቀጠል ባይችሉ፥ ጠቅላላ ጉባዔዉ ተጠርቶ ተተኪዎች እስኪመረጡ ድረስ፥ የስራ አስፈጻሚ ኮሚቴዉን ስራ ይመራል

ረ. የአባላትን የስም ዝርዝርና ወቅታዊ የሆነ ሙሉ አድራሻ ይይዛል። አባላትን የተመለከቱ የግል ኢንፎርሜሽኖች ያለፈቃዳቸዉ ወይም የመንግስት ህግ ከሚያዘዉ ዉጭ ከማኅበሩ ዉጭ ላሉ ግልሰቦች ወይም ድርጅቶች እንዳይደርስ ከፍተኛ ጥንቃቄ ያደርጋል።

ሰ. ከማኅበሩ የስራ እንቅስቃሴ ጋር በተያያዘ መንገድ በማኅበሩ ዌብ ሳይት፥ መጽሔቶችና ሌሎች የመገናኛ ብዙሃን ላይ አባላትን ወይም ልጆቻቸዉን የተመለከቱ ኢንፎርሜሽኖችን ማዉጣት ሲያስፈልግ አባላት ፈቃድ የሚጠየቁበትን ፎርም ይይዛል፤ አስፈላጊዉ ፈቃድም መገኘቱን ይቆጣጠራል።

ሸ. በማኅበሩ ሊቀመንበር የሚሰጡትን ሌሎች ተመሳሳይ ተግባራትን ያከናዉናል።

18.5 የማኅበሩ ሂሳብ ሹም የሚከተሉት ተግባራት ይኖሩታል፤

ሀ. ከስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ አባላት ጋር በመካከር፥ የማህበሩን በጀት ያዘጋጃል፤ በንዑሳን ኮሚቴዎች የሚቀርቡለትን ዓመታዊ በጀቶች ከአጠቃላይ የማህበሩ በጀት ጋር ያጣጥማል፤ ከስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ሊቀመንበር (የቦርዱ ጸሀፊ) ጋር በመሆን የማህበሩን አጠቃላይ በጀት ለቦርዱ ያቀርባል፤ የማኅበሩ አጠቃላይ በጀት በጠቅላላ ጉባዔዉ መጽደቅ ይኖርበታል፤ ዝርዝር በጀቶችን ግን ቦርዱ መርምሮ ያጸድቃል።

ለ. በቦርዱ የጸደቀዉ በጀት፥ በስራ ላይ በትክክል መዋሉን ይከታተላል፤ ችግሮችን ይገመግማል።

ሐ. ከገንዘብ ያዢ/ንብረት ኃላፊና ከኦዲት ኮሚቴ ጋር በመሆን የማኅበሩን የሂሳብና የንብረት ቅጾችን ያዘጋጃል።

መ. ከማኅበሩ የገንዘብ ያዢ/ንብረት ኃላፊ የወጭ ዝርዝሮችን ወቅታዊ በሆነ መንገድ በመሰብሰብ የገቢ- ወጭ ዘገባንና በየስድስት ወሩ በማዘጋጀት ለሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ያቀርባል።

ሠ. ንዑሳን ኮሚቴዎችና ጊዜያዊ ኮሚቴዎች ወጪና ገቢን ማኅበሩ ባዘጋጀዉ ሠነዶችና ቅጾች በትክክል መሞላታቸዉንና በተግባር ላይ መዋላቸዉን ይቆጣጠራል።

ረ. ከማኅበሩ የገንዘብ ያዥና ንብረት ኃላፊ ጋር በመተባበር የተለያዩ ጨረታዎችን እንዳስፈላጊነቱ ያዘጋጃል፤ ያካሂዳል።

ሰ. አመታዊ የገቢ- ወጭ ዘገባንና የገንዘብና ንብረት ማመዛዘኛን (Income Statement and Balance Sheet) ያዘጋጃል፤ በአመታዊዉ አጠቃላይ የስራ ሪፖርት ዉስጥ እንዲካተት ያደርጋል።

ሸ. የማህበሩን አመታዊ የታክስ ፋይል (tax return) ያዘጋጃል።

ቀ. ሌሎች በማኅበሩ ሊቀመንበር የሚሰጡትን ተመሳሳይ ተግባሮች ያከናዉናል።

18.6 የማኅበሩ ገንዘብ ያዢ/ንብረት ኃላፊ የሚከተሉት ተግባራት ይኖሩታል፤

ሀ. በዘመናዊ የገንዘብና የንብረት አያያዝ ዘዴ የማኅበሩን ገንዘብ፥ ሀብትና ንብረት ይይዛል፤ ይቆጣጠራል። የማኅበሩ ቋሚና ተንቀሳቃሽ ንብረቶች ተገቢዉን እንክብካቤ እንዲያገኙና አስፈላጊ ጥገናዎችን በወቅቱ እንዲያገኙ ያደርጋል።

ለ. ከሂሳብ ሹሙና ከኦዲት ኮሚቴ ጋር በመሆን የማኅበሩን የሂሳብና የንብረት ቅጾች ያዘጋጃል።

ሐ. የአባልነት መመዝገቢያና ዓመታዊ ክፍያን ይሰበስባል።

መ. ሌሎች ለማኅበሩ ገቢ ሊሆኑ የሚገባቸዉን ሀብትና ንብረት እየተቆጣጠረ ገቢ እንዲሆኑ ያደርጋል።

ሠ. እያንዳንዱ ወጭና ገቢ በአስፈላጊዉ ቅጽ መታጀቡን ያረጋግጣል፤ ይቆጣጠራል።

ረ. ማንኛዉም ገቢና ወጪ ኃላፊነትና ሥልጣን በተሰጠዉ ተመራጭ አማካኝነት እንዲፈጸም ያደርጋል።

ሰ. ከላይ በአንቀጽ 18.2(ረ)ና 18.3(ሀ) መሠረት ከሊቀመንበሩ ወይም ከምክትል ለቀመንበሩ ጋር በመሆን ቼኮችን ይፈርማል።

ሸ. የገቢና ወጭ ዝርዝር በማዘጋጀት ለሂሳብ ሹሙ ያቀርባል።

ቀ. ለዕለት-ተዕለት ተግባር የሚያስፈልጉትን የጽህፈትና ሌሎች ቁሳቁሶች ያቀርባል፤ ይቆጣጠራል። ለጥቃቅን ወጮች የሚሆን ገንዘብ (Petty Cash) ይይዛል።

በ. ሌሎች በማኅበሩ ሊቀመንበር የሚሰጡትን ተግባሮች ያከናዉናል።

## አንቀጽ 19 የማህበሩ ንዑስ ኮሚቴዎች፥ ተግባርና ኃላፊነት

19.1 ማኅበሩ ተጠሪነታቸዉ ለሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ የሆኑ፥ በሥራ አስፈጻሚ ኮሚተዉ የሚቋቋሙና፥ የአገልግሎት እድሜያቸዉ ሁለት አመት የሆነ የሚከተሉት ንዑሳን ኮሚቴዎች ይኖሩታል፤

- የባሕል፥ የኪነጥበብና ሥነ- ጽሑፍ ኮሚቴ
- የገቢ ምንጭ ኮሚቴ
- የሕዝብ ግንኙነት ኮሚቴ
- የስፖርትና የወጣቶች ጉዳይ ኮሚቴ
- የሴቶች ጉዳይ ኮሚቴ
- የልማትና እርዳታ ኮሚቴ

### 19.2 የባሕል፥ የኪነጥበብና ሥነ- ጽሑፍ ኮሚቴ ተግባርና ኃላፊነት

ሀ. ይህ ንዑስ ኮሚቴ አምስት አባላት ይኖሩታል፤ የስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ የባሕል፥ የኪነጥበብና ሥነ-ጽሑፍ ኃላፊ የዚህ ኮሚቴ መሪ ይሆናል።

ለ. ከላይ በአንቀጽ 4.3 መሰረት አባላት የፈጠራ ችሎታቸዉን በመጠቀም የኢትዮጵያን የተለያዩ ባሕሎችና ታሪኮች በሥነ-ጽሑፍ፥ በግጥም፥በሥዕል፥ በድራማ ፥ በሙዚቃ፥ ወዘተ እንዲያንፀባርቁ ያበረታታል፥ አቅም በፈቀደ መጠን ሁኔታዎችንና አጋጣሚዎችን ያመቻቻል። ለዚሁም የሚረዳ መድረክ ለመፍጠር በዓመት ሁለት ጊዜ "የኢትዮጵያ ምሽት" የተሰኘ ፕሮግራም ያዘጋጃል።

ሐ. የኢትዮጵያን የባሕልና የወግ ዕቃዎች በማሰባሰብና በመድረክ (በሙዚቃ)ና በኤግዚብሽን ገለጻ የሚሳተፉት አባላትና ተሳታፊ ግለሰቦች በቂ ስልጠና እንዲኖራቸዉ በማድረግ፥ በየዓመቱ በኤድመንተን ከተማ በሚደረገዉ የሄሪቴጅ ፌስቲቫል ላይ ማህበሩ በበቂ ዝግጅት እንዲሳተፍ ያደርጋል። ለዚህም ማህበሩ በሚመድበዉ በጀት በበዓሉ ወቅት ለኤግዚብሽን የሚቀርቡ ዕቃዎች የተሟሉ፥ የሚሰሩና በጥሩ ይዞታ ላይ ያሉ መሆናቸዉን ያረጋግጣል፤ ያረጁ ወይም የማይሰሩ ዕቃዎች በወቅቱ እንዲተኩ ያደርጋል።

መ. አባላት፥ የኢትዮጵያን ታላላቅ ታሪካዊ ቀኖችን (ለምሳሌ የአድዋ ድል መታሰቢያን)ና የኢትዮጵያን አዲስ አመት በዓል በህብረት የሚያከብሩበትን ዝግጅት ያደራጃል፤ ያከናዉናል።

ሠ. ሌሎች በዓሎችን (ምሳሌ የእናቶች ቀን) ከስራ አስፈጻሚ ኮሚቴዉ ጋር በመመካከር እንዳስፈላጊነቱ ያዘጋጃል።

ረ. አባላቱና ልጆቻቸዉ ቢያንስ የኢትዮጵያን ብሄራዊ ቋንቋ እንዲማሩ ወይም እንዳይረሱ ያበረታታል፤ አቅም በፈቀደ መጠንም የትምህርት ፕሮግራሞችን ያዘጋጃል።

ሰ. የማህበሩን አመታዊ መጽሔት (Year Book) ያዘጋጃል።

ሸ. ሌሎች የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴዉ እንደስፈላጊነቱ የሚሰጠዉን ተግባሮች ያከናዉናል።

19.3 **የገቢ ምንጭ ኮሚቴ ተግባርና ኃላፊነት**

ሀ. ይህ ንዑስ ኮሚቴ አምስት አባላት ይኖሩታል፤ የሚመራዉም በስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ የሂሳብ ሹም ይሆናል።

ለ. ለማኅበሩ የገቢ ምንጭ የሚሆኑ የተለያዩ ዝግጅቶችን በማደራጀት ተግባራዊ ያደርጋል።

ሐ. ከሌሎች የማኅበሩ ኮሚቴዎች ጋር በመሆን ልዩ ልዩ የገቢ ምንጮችን በመፍጠር (ለምሳሌ ቢንጎ፥ ካሲኖ) የማኅበሩ ገቢ የሚያድግበትን ዘዴ ይተልማል፤ ተግባራዊም ያደርጋል።

መ. ከሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ እንደስፈላጊነቱ የሚሰጡትን ልዩ ልዩ ተመሳሳይ ተግባሮችን ያከናዉናል።

19.4 **የሕዝብ ግኑኝነት ኮሚቴ ተግባርና ኃላፊነት**

ሀ. ይህ ኮሚቴ አምስት አባላት ሲኖሩት፥ የሚመራዉም በስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ የህዝብ ግኑኝነት ሃላፊ ይሆናል።

ለ. የማኅበሩን ዓላማና ተግባር ለመንግሥታዊና ግላዊ ድርጅቶች ያስተዋዉቃል።

ሐ. በአንቀጽ 3.2 መሠረት አዲስ ወደ ኤድመንተን የሚመጡ ኢትዮጵያዉያን ማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ ዕርዳታ እንዲያገኙ ከኢሚግሬሽንና ከካቶሊክ ሶሻል ሰርቪስ እንዲሁም ከሌሎች መሰል ድርጅቶች ጋር ግኑኝነት በመፍጠር ይሰራል።

መ. በአመት አንድ ጊዜ ታትሞ የሚወጣዉን የማኅበሩን መጽሔት (Year Book) ለማዘጋጀት ከባህል፥ ኪነጥበብና ሥነ ጽሑፍ ኮሚቴ ጋር ይተባበራል።

ሠ. በኤድመንተን የሚኖሩና አዲስ የሚመጡ ኢትዮጵያዊያን የማኅበሩን ዓላማ እንዲያዉቁና ንቁ ተሳታፊ እንዲሆኑ ለማድረግና አባላትን ለመጨመር ይጥራል።

ረ. አዲስ የሚመጡ ኢትዮጵያዉያንን ልዮ ዝግጅት በማድረግ ከአባላት ጋር ያስተዋዉቃል።

ሰ. የማኅበሩን የስራ እንቅስቃሴ ለማስተዋወቅ፥ የስብሰባ ጥሪዎችን በተቀላጠፈ ሁኔታ ለማድረግና፥ የማኅበሩን አባላት የሚያስተሳስሩና ሌሎች የማህበሩን አላማዎች ለማራመድ የሚጠቅሙ ባህላዊ፥ ኪነጥበባዊና ሌሎች ጽሑፎችንና ዝግጅቶችን ለማስተላለፍ የሚረዱ የመገናኛ ብዙሃንን (ለምሳሌ፥ የሬዲዮ ጣቢያ) ለማግኘት ይጥራል። የስራ አስፈጻሚ ኮሚቴዉ በሚያወጣዉ መመሪያ መሰረትም በጥቅም ላይ ያዉላል።

ሸ. ሌሎች በሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ የሚሰጠዉን መሰል ተግባሮች ያከናዉናል።

19.5 **የስፖርትና የወጣቶች ንዑስ ኮሚቴ ተግባርና ኃላፊነት**

ሀ. ይህ ኮሚቴ አምስት አባላት ይኖሩታል፤ የሚመራዉም በስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ የስፖርትና ወጣቶች ጉዳይ

ሃላፊ ይሆናል።

ለ. በተለያዩ ስፖርታዊ ዝግጅቶች አማካኝነት ኢትዮጵያዉያን እንዲገናኙ ፥እንዲተዋወቁና በአባላትም መካከል መግባባት እንዲጠነክር አስፈላጊዉን ጥረት ያደርጋል።

ሐ. በሰሜን አሜሪካና ኢትዮጵያ ዉስጥ ካሉ ኢትዮጵያዊ የስፖርት ቡድኖችና ድርጅቶች ጋር ግንኙነት ይፈጥራል። አቅም በፈቀደ መጠንና እንዳመቺነቱ በካናዳ ዉስጥ በሚዘጋጁ የስፖርት ዉድድሮች (Tournament) ማኅበሩ የሚሳተፍበትን መንገድ ያጠናል፤ ያስተባብራል።

መ. የስፖርትን ጠቃሚነት በአባላቱ መካከል ያስተዋዉቃል፤ ስፖርት ለጤንነት በሚል መርህ በአመት አንድ ጊዜ የሚከበር የስፖርት ቀን ያዘጋጃል።

ሠ. ሌሎች በሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ የሚሰጠዉን መሰል ተግባሮች ያከናዉናል

19.6 የሴቶች ጉዳይ ኮሚቴ ተግባርና ኃላፊነት

ሀ. ይህ ኮሚቴ አምስት አባላት ይኖሩታል፤ የሚመራዉም በስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ የሴቶች ጉዳይ ሃላፊ ይሆናል።

ለ. የማኅበሩ ሴት አባላት በማኅበሩ ዉስጥ የሚኖራቸዉን ተሳትፎ ከፍ ለማድረግ ይጥራል፤ በሴትነታቸዉ በቂ ተሳትፎ እንዳያደርጉ የሚያደርጋቸዉ ችግሮች ቢኖሩ ችግሮቹ የሚወገዱበትን መንገድ ያጠናል፤ ከስራ አስፈጻሚ ኮሚቴዉ ጋር በመሆን መፍትሄዎችን ይፈልጋል።

ሐ. የማኅበሩ ሴት አባላት በህብረተሰቡ ዉስጥ፥ በስራ ቦታና፥ በቤተሰብ ደረጃ ስላለባቸዉ የተለዩ ኃላፊነትና ችግሮች መወያዬት የሚችሉበትን መድረክ ያዘጋጃል፤ የሚረዳዱበትን መንገድ ያጠናል።

መ. ሌሎች በሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ የሚሰጡ ተግባሮች ያከናዉናል።

19.7 የልማትና እርዳታ ኮሚቴ ተግባርና ኃላፊነት

ሀ. ይህ ኮሚቴ አምስት አባላት ይኖሩታል፤ የሚመራዉም በስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ም/ሊቀመንበርይሆናል።

ለ. ማኅበሩ በኢትዮጵያ ዉስጥ በእርዳታና፥ የልማት እንቅስቃሴዎች ዉስጥ ሊሳተፍ የሚችልባቸዉን መንገዶችና አቅሞች እያጠና በስራ አስፈጻሚ ኮሚቴዉ በኩል ለቦርዱ እንዲደርስ ያደርጋል።

ሐ. መኅበሩ በኤድመንተንና አካባቢ በሚካሄዱ ማህበራዊና የልማት እንቅስቃሴዎች የሚሳተፍባቸዉን ሁኔታዎች ያጠናል፤ በስራ አስፈጻሚ ኮሚቴዉ በኩልም ለቦርዱ እንዲደርስ ያደርጋል።

መ. ሌሎች በሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ የሚሰጡ ተግባሮች ያከናዉናል።

አንቀጽ 20 የኦዲት ኮሚቴ ተግባርና ኃላፊነት

ሀ. ይህ ኮሚቴ ሦስት አባላት ያሉት ሲሆን በጠቅላላዉ ጉባኤ ተመርጦ ይቋቋማል። ተጠሪነቱም ለጠቅላላ ጉባዔዉ ይሆናል።

ለ. የዚህ ኮሚቴ አባላት በሌላ ኮሚቴ ዉስጥ ተመርጠዉ አይሰሩም።

ሐ. ቢያንስ አንዱ የኮሚቴ አባል ዘመናዊ የሂሳብ አሠራርና አያያዝ ትምህርት የቀሰመ ወይም በሙያዉ በቂ

ልምድ ያለዉ መሆን አለበት።

መ. የኮሚቴዉ የኃላፊነት ዘመን ሁለት ዓመት ይሆናል።

ሠ. ከሂሳብ ሹሙና ከገንዘብ ያዡና ንብረት ኃላፊ ጋር በመመካከር የማኅበሩን የሂሳብና የንብረት ቅጾችን በኃላፊነት ያዘጋጃል።

ረ. የዉስጣዊ አሰራሩን መመሪያ በማዘጋጀት በቦርዱ ያስጸድቃል።

ሰ. የማህበሩን የገንዘብ፥ የኃብትና የንብረት አያያዝና አጠቃቀም በየሶስት ወሩ ይመርምራል፤ ሆኖም አስፈላጊ መስሎ በታዬዉጊዜ ድንገተኛ ምርመራ ማድረግ ይችላል፤ ለዚህም የማህበሩ አባላትና ተመራጮች ሙሉ ትብብር ማድረግ ይጠበቅባቸዋል።

ሸ. በአመት አንድ ጊዜ የጠቅላላ ኦዲት ሪፖርት በማዘጋጀት ለቦርዱ ያቀርባል፤ ቀጥሎም ለጠቅላላ ጉባዔዉ ያቀርባል።

## አንቀጽ 21 ኮሚቴዎች የራሳቸውን የስራና የኃላፊነት መመሪያ ስለማዘጋጀት

በዚህ መተዳደሪያ ደንብ ዉስጥ የተጠቀሱት ኮሚቴዎችም ሆኑ ሌሎች የስራ አስፈጻሚ ኮሚቴዉ እንዳስፈላጊነቱ ወደፊት የሚያቋቁማቸዉ ኮሚቴዎች የየራሳቸዉን የስራና የኃላፊነት ዝርዝር መመሪያ በማዘጋጀትና በስራ አስፈጻሚ ኮሚቴዉ በማስጸደቅ መጠቀም ይችላሉ። የስራ አስፈጻሚ ኮሚቴዉ ዝርዝር የሃላፊነት መመሪያዎች በዚህ መተዳደሪያ ደንብ ዉስጥ ከተመለከቱት ሕግጋት ጋር እንዳይጋጩ በጥንቃቄ ይመረምራል።

## አንቀጽ 22 የምርጫ አፈጻጸም

21.1 የምርጫ አስፈጻሚ ኮሚቴ

ሀ. ይህ ኮሚቴ በጠቅላላ ጉባዔዉ የሚመረጡ ሦስት አባላት ይኖሩታል። የኃላፊነት ዘመኑም ሁለት አመት ይሆናል።

ለ. ለዚህ ኮሚቴ የሚመረጡ አባላት ቢያንስ ለሁለት ዓመት በአባልነት የቆዩ፥ የማኅበሩን ዓላማና ተግባር እንዲሁም የመተዳደሪያ ደንቡን ጠንቅቀዉ የተረዱ መሆን አለባቸዉ።

ሐ. በጠቅላላ ጉባኤዉ የሚያቋቋሙ ኮሚቴዎች የምርጫ ስርአት በዲሞክራሲያዊ መንገድ እንዲፈጸም ያደርጋል።

መ. በምርጫዉ ወቅት ለአባላት የኮሚቴዎችንና የተመራጮችን ኃላፊነት በተመለከተ በቂ ማብራሪያ በመስጠት ምርጫዉ ግልጽ እንዲሆን ያደርጋል።

22.2 የምርጫ አፈፃፀም ሥርዓት

ሀ. የኮሚቴዎች ምርጫ ለማካሄድ፥ ቢያንስ የማኅበሩ 2/3ኛ አባላት መገኘት አለባቸዉ። ሆኖም በመጀመሪያ የምርጫ ጥሪ 2/3ኛዉ የማህበሩ አባላት ሳይገኙ ቢቀር፥ በሁለተኛዉ የምርጫ ጥሪ ከሃምሳ በመቶ በላይ የሚሆኑ አባላት ከተገኙ ምርጫዉ ይካሄዳል።

ለ. ለእያንዳንዱ የስራ እስፈጻሚ ኮሚቴ የምርጫ ቦታ ቢያንስ ሁለት ግለሰቦች ለዉድድር መቅረብ አለባቸዉ። ለሰባቱ የቦርድ የምርጫ ቦታዎች ቢያንስ አስር ግለሰቦች ለዉድድር መቅረብ አለባቸዉ። ይሁንና በምርጫ ዉስጥ ለመግባት ፈቃድ እንደሚያሳዩት ግለሰቦች ቁጥር መብዛት ወይም ማነስ ሁኔታ የምርጫ አስፈጻሚ ኮሚቴዉ ቁጥሩን በተመለከተ አንድ ዉሳኔ በማድረግ የኮሚቴ ቦታዎች እንዲሟሉ ያደርጋል።

ሐ. ለምርጫ የሚቀርቡ ዕጩዎች ስም ዝርዝር ቢይፋ እንዲታወቅ ከተደረገ በኋላ ምርጫዉ በሚስጥር ድምጽ አሰጣጥ (Secrete Ballot) ደንብ ይካሄዳል።

መ. ለቦርዱ ፕሬዚዳንትነትና ለስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ሊቀመንበርነት የሚመረጡ አባላት፥ በመጀመሪያ ዙር ምርጫ ያገኙት ድምጽ፥ ተወዳዳሪዎቻቸዉ ካገኙት ድምጽ ድምር መብለጥ አለበት፤ ይህ ባልሆነበት ወቅት፥ አንደኛና ሁለተኛ የወጡት እጩዎች ለሁለትኛ ዙር ምርጫ ይቀርባሉ። ለሌሎች የኃላፊነት ቦታዎች የተወዳደሩ እጩዎች ለሁለተኛ ዙር ምርጫ የሚቀርቡት፥ ከፍተኛዉን ድምፅ እኩል ያገኙ ተወዳዳሪዎች ሲኖሩ ብቻ ነዉ።

22.3 የመምረጥና የመመረጥ መብት

ሀ. ለኮሚቴ አባልነት ለምርጫ የሚቀርብ ማንኛዉም ግለሰብ ቢያንስ ለአንድ አመት የማኀበሩ አባል ሆኖ የቆየ/የቆየች መሆን አለበት/አለባት።

ለ. የኮሚቴ አባላት ምርጫ ላይ ድምጽ ለመስጠት አንድ ግለሰብ ቢያንስ ለስድስት ወር የማኀበሩ አባል ሆኖ የቆየ/የቆየች መሆን አለበት/አለባት።

ሐ. ተመራጮች፥ የማህበሩን አላማ፥ ህግና ደንብ ጠንቅቀዉ የሚያዉቁ እንዲሆኑ ይጠበቃል።

22.4 ተተኪ አባላትን ስለመምረጥ

በተለያዩ ምክንያቶች ተመራጮች ሥራቸዉን መሥራት ካልቻሉ፥ የምርጫ ደንብን በመከተል ሌሎች አባሎች ተመርጠዉ ይተኳቸዋል።የተተኪ አባላት ምርጫ ቢዘገይ በሚቀጥለዉ ጠቅላላ ጉባኤ ስብሰባ ይሆናል።

22.5 ደግሞ ስለመመረጥ

የማንኛዉም ኮሚቴ አባል ከሁለት ጊዜ በላይ ለተመሳሳይ የኃላፊነት ቦታ በዕጩነት ለምርጫ ሊቀርብ አይችልም። ከአንድ ዓመት ቆይታ በኋላ ግን እንደገና በዕጩነት መቅረብ ይችላል።

## አንቀጽ 23 የጠቅላላ ጉባኤዉ ስብሰባ

የጠቅላላ ጉባኤዉ ስብሰባ በስድስት ወር አንድ ጊዜ ይሆናል። ለዚሁም ስብሰባ ቦርዱ ከሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴዉ ጋር በቂ ዝግጅት በማድረግ የስብሰባዉን ቦታና ሰዓት ቀደም ብሎ ለአባላት ያስታዉቃል። ቦርዱ (ወይም ከላይ በአንቀጽ 17(ሐ) የግርጌ ማስታወሻ 5 መሰረት የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴዉ) አስቸኳይ ጉዳይ ሲያጋጥመዉ የስብሰባዉን አጀንዳ በማስታወቅ ጠቅላላ የአባላት ስብሰባ በማንኛዉም ጊዜ ሊጠራ ይችላል።

## አንቀጽ 24 አስተያየትና ቅሬታን ስለመግለጽ

ሀ. ማንኛዉም የማኀበሩ አባል በተናጠል ወይም ከሌሎች አባላት ጋር በጋራ በመሆን የማኀበሩ አሰራርና አፈጻጸም በተመለከተ ቅሬታ ወይም አስተያየት ሲኖረዉ ወይም የማህበሩ ተመራጮች የተጣለባቸዉን ኃላፊነት በብቃት አልተወጡም ብሎ ሲያምን፥ ቅሬታዉን ለቦርዱ በጽሁፍ የማቅረብ መብት አለዉ።

ለ. አንድ አባል፥ አንድ ወይም ከዚያ በላይ ተመራጮች ከአገልግሎት ቦታቸዉ መነሳት አለባቸዉ ብሎ ሲያምን የአባላቱን አስር በመቶ የድጋፍ ፊርማ በማሰባሰብ ጥያቄዉን በጽሁፍ ለቦርዱ ማቅረብ ይችላል። ቦርዱም የቀረበለትን ጥያቄ መርምሮ፥ በቂ ምክንያት አለ ብሎ ሲያምን ጉዳዩን ከአማራጭ አስተያየት ጋር ለጠቅላላ ጉባዔዉ ያቀርባል፤ እስከዚያ ድረስም፥ እንዳስፈላጊነቱ ጊዜያዊ ዉሳኔ ሊያሳልፍ ይችላል።

**አንቀጽ 25 አረካካቢ ኮሚቴ**

ሀ. የማኅበሩ የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ የሥራ ዘመን ሲፈፀም፥ የማህበሩን ገንዘብ፥ ሃብትና ንብረት ተቆጣጥሮ ለአዲስ ተመራጮች የሚያረካክብና ለጠቅላላ ጉባኤዉ ሪፖርት የሚያቀርብ በጠቅላላ ጉባኤዉ የሚመረጥ ሦስት አባላት ያሉት የሽግግር ጊዜ አረካካቢ ኮሚቴ በየሁለት ዓመቱ ይቋቋማል።

ለ. የአረካካቢ ኮሚቴዉ የስራ ዘመን ከምርጫ ጊዜ ቀጥሎ እስከሚኖረዉ የመጀመሪያ ጠቅላላ ጉባዔ ስብሰባ ድረስ ይሆናል።

**አንቀጽ 26 የማኅበሩ የሂሳብ ዓመት**

የማኅበሩ የሂሳብ ዓመት ከመስከረም 1 (September 11) እስከ ጳጉሜ 5 ወይም 6 (September 10) ይሆናል።

## ክፍል አስራአንድ

**አንቀጽ 27 የማኅበሩን ህግና ደንብ ስለማሻሻል**

ከላይ በአንቀጽ 16(መ) መሰረት ቦርዱ ማሻሻያዎችን እያጠና ለጠቅላላ ጉባኤዉ ሲያቀርብና ጠቅላላ ጉባኤዉ ሲያምንበት ብቻ የማህበሩ ህግና ደንብ ይሻሻል። የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴዉና ሌሎች ኮሚቴዎች ማሻሻያዎችን በቦርዱ በኩል ማቅረብ ይችላሉ። ማንኛዉም አባል ከሌሎች አስር አባላት ጋር በጋራ በመሆን ማሻሻያዎችን በቦርዱ በኩል ማቅረብ ይችላል።

**አንቀጽ 28 ማኅበሩን ስለማፍረስ**

ሀ. በአንድ ወቅት በተለያዩ ምክንያቶች የዚህ ማኅበር ሕልዉና አስፈላጊ ከማይሆንበት ሁኔታና ደረጃ ቢደርስ በአልበርታ የማህበራት ህግ (Societies Act) መሰረት ከጠቅላላዉ አባላት ቢያንስ 75 በመቶ የሚሆኑት በሚገኙበት የጠቅላላ ጉባአዉ ስብሰባ በሚተላለፍ ዉሳኔ መሠረት ማኅበሩ ይፈርሳል።

ለ. ከላይ በ"ሀ" መሰረት ማኅበሩ ሲፈርስም የማኅበሩ ገንዘብ፥ ሃብትና ተንቀሳቃሽና የማይንቀሳቀስ ንብረት ጉባኤዉ ለሚመርጠዉ ሰብዓዊና በጎ አድራጎት ድርጅት/ድርጅቶች ይሰጣል።

**አንቀጽ 29 አበልና ሌላ ክፊያ**

ሀ. የማኅበሩን ዓላማ ከግብ ለማድረስ በማንኛዉም ኮሚቴ ዉስጥ የሚሰሩ አባላትና ኃላፊዎች ለማኅበሩ ለሚያበረክቱት አገልግሎት ምንም ዓይነት ደመወዝ ወይም ክፍያ ሊጠይቁ አይችሉም። ሆኖም ግን ከማኅበሩ የስራ እንቅስቃሴ የተነሳ ከከተማ ዉጭ ለሚደረጉ የጉዞ ወጪና ሌሎች ወጪች፥ እንዳስፈላጊነቱ ቦርዱ በሚያጸድቀዉ የወጭ ስኬል መሰረት ወጭ ይደረጋል። ከአልበርታ ዉጭ የሚደረጉ ጉዞዎች በቦርዱ መጽደቅ አለባቸዉ።

ለ. በአልበርታ ዉስጥ ለሚደረጉ ጉዞዎችና ሌሎች ጊዜያዊና ጥቃቅን ወጪች የስራ አስፈጻሚ ኮሚቴዉ ሊቀመንበር በሚያዘዉ መሰረት ወጭ ይደረጋል። ጥቃቅን ወጪች፥ የስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ሊቀ-መንበሩ እንግዶችን ለመቀበል ወይም እንዳስፈላጊነቱ መጠነኛ ግብዣ ለማድረግ የሚያስፈልገዉን ወጭ ይጨምራሉ።

**አንቀጽ 30 ኃላፊነትና ተጠያቂነት**

ሀ. በማንኛዉም የማኅበሩ የሥራ ድርሻና ኃላፊነት የተመደቡ ተመራጮች የማኅበሩን ሕግና ደንብ እንዲሁም

በአልበርታ የማኅበራት ሕግ (Societies Act) ተከትለዉ የማኅበሩን አንድነት በመጠበቅ የመሥራት ኃላፊነትና አደራ የተጣለባቸዉ ሲሆን ተመራጮች በማወቅም ሆነ ባለማወቅ በተናጠልም ወይም በጋራ ለሚያደርሱት ጥፋትና ጉዳት ተጠያቂዎች ናቸዉ።

ለ. አንድ አባል ወይም ተመራጭ የማህበሩን ስራ እያካሄደ ባላበት ወቅት ለሚፈጥረዉ ጥፋትና ጉዳት በህግ ተጠያቂ ቢሆን፥ ማህበሩ ኃላፊነት አይወስድም፤ ሆኖም ማህበሩ እንዳስፈላጊነቱ የበጎ ፈቃድ ርዳታ ሊያደርግ ይችላል።

**አንቀጽ 31 የዚህ ደንብ ተፈጻሚነት**

ይህ ደንብ የማኅበሩ አባላት 2/3ኛዉ ተገኝተዉ በዝርዝር ከተወያዩበትና ካፀደቁበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል።